

# ዓለም በቃኝ አለ

**(ለጋሼ ኃይሉ ገሞራው መታሰቢያ)**

ሁሌ እንደጠየቀ፣ እንደመረመረ
የሕይወትን ምስጢር እንደሰረሰረ
ሰባት አሥርታትን ከኛ ጋር የኖረ
ገሞራው እምቢባይ፣ ዛሬስ አመረረ
ዓለም በቃኝ ብሎ፣ ድንገት ተሰወረ፤

በግእዝ በቺና፣ በኖሽክ በስቬንስኩ
በእንግልጣን አንጋሩ፣ ባማርኛ መስኩ
ሁሌ እንደተቀኘ፣ ሁሌ እንደፈለመ
ሕዝብ እንዳስተማረ፣ ቅኔ እንደሸለመ
እንደከፋው ኖሮ፣ እንደከፋው ሄደ
አርባ ዓመታት ሙሉ፣ እንደተሰደደ፤

አገሬን ወገኔን፣ ናፈቅሁኝ እንዳለ
ከሥርዓት ከዘመን እንደተቋሰለ
ሐዋሪያው ኃይሉ፣ እንደወጣ ቀረ
ሰው መሆን ሸክላነት፣ ምንጊዜም አልቀረ፤
ማን አለ ከደጁ፣ ማንስ ለኛ ቀረ
ዓለም በቃኝ ብሎ፣ ጋሼም ተሰወረ፤

-በአበራ ለማ (ኦስሎ፣ ሕዳር 3/2007